- በአገልግሎቱ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ስለማይሠራ፤ አገልግሎቱ ብቻውን ከአካባቢው ጠባይና ልማድ የማይለይ ይሆናል።

በዚህም መካከል፤ <u>የሚጣደፉ የጥፋት እጆች፤ ለተንኮል የሚዘጋጁ የመናፍስት ወረራዎች፤ የሰው ልጆችን ሕይወት ያጎዳሉ</u>። ለእግዚአብሔር አምልኮት ከሌለን፤ ጥፋቶች አይቆሙም፤ የተወሳሰቡ ችግሮች ኑሮዋችን ይሆናሉ።

የፍዳ መንገዶችንም እንዲሁ ወደ ብርሃን ሳይመጡ ይቀሩና፤ ትውልዱም በጨለማ አስተሳሰብ የዲያብሎስ መጫዎቻ ይሆናል። የእግዚአብሔር አምልኮት የሌለበት ሕይወትና አገልግሎት፤ እንዲሁም የምዕመናን ኑሮ ሲታይ፤ ዛሬ በብዙ አቅጣጫዎች የተከፈቱ መንፈሳዊ ውጊያዎች እንዳሉ ያመለክታሉ።

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔርን ሳያመልኩ ማገልገል ማለት፤ እንዴት እንደሆነ በዔሊና በቤተሰቦቹ እንዲሁም በሚመራው በእስራኤል ሕዝብ ላይ የታየውን ውድቀት በግልጽ ያስተምረናል።

ዔሊ በዘመኑ እጅግ ታላቅ ከሚባሉ አባቶች መካከል የሚመደብ፤ ካህን፤ ፈራጅም፤ ዳኛም፤ መሪም ሆኖ የኖረ ሰው ነበር።

ዔሊ የሚለው ቃል ቀጥታ ከእብራይስጥ ወደ አማርኛ ሲለወጥ፤ በሁለት መዝገበ ቃላት እንደሚከተለው ተገልጿል።

አንዱ <u>‹‹ኤሎሄ አምላኬ››</u> ከሚለው ቃል ጋር የሚያያዝ ሲሆን፤ ሁለተኛው ትርጉም ደግሞ፤ <u>‹‹አሣራጊ፤ ጸሎት ወደ ሰማይ አምላክ አቅራቢ››</u> ማለት እንደሆነ ተቀምጧል። ዔሊ በክሕነት ዓለም ውስጥ ሲያገለግል የኖረ መንፈሳዊ በረከትን የተቀበለ ሰው ሲሆን፤ በእስራኤል እሱ ከሚባሉ ታላላቅ የመንፈሳዊ የቃል ኪዳን ሰዎች መካከልም፤ አንዱ ነበር።

በጣም የሚያሳዝነውና የሚገርመው ግን፤ ዔሊ የአምልኮት ጊዜ የሌለው መሆኑ ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ በሕይወቱ ብዙ ነገሮች ተበላሽተውበታል።





በእስራኤል ላይ የደረሱት ታላላቅ ውድቀቶች ጎልተው የታዩትና በታሪክ ውስጥ የሚያሳዝን ምዕራፍ የተመዘገበበት፤ በዚህ የዔሊ ዘመን ውስጥ ነው።

ይህም፤ አገልግሎቱ በመንፈሳዊ ቅድስና በማስተማር ሁሉ አካቶ የእግዚአብሔርን ሕዝብ በእግዚአብሔር ጸጋ መምራትና በአምልኮት ራእይ ማሳደግ አለመቻሉ ነው።

እግዚአብሔርን እያመለኩ፤ ለሕጉና ለክብሩ እየተገዙ በእግዚአብሔር ቸርነት ውስጥ በረከትን በሙላት እንዲቀበሉ፤ አምላክ ሥልጣን ሰጥቶ ነበር።

እግዚአብሔር ለዘለዓለም የሚወደውን ሕዝብ፤ ዔሊ መምራት ጀምሮ፤ ከቃል ኪዳን በረከትም ውስጥ፤ ብዙ ነገሮችን እንደተቀበለ 1ኛ ሳሙ. 1÷2 ላይ የታላቁን ካህን የዔሊን መንገድ ያሳየናል።

## 8.1 <u>ለራሱ መልስ የሌለው አገልግሎት፤</u>

**‹‹ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ ይሆናሉ፣ ገንዘብን የሚወዱ፣ ትምክህተኞች፣ ትዕቢተኞች፣ ተሳዳቢዎች፣ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፣ የማያመሰግኑ፣ ቅድስና የሌላቸው፣ ፍቅር የሌላቸው፣ ዕርቅን የማይሰሙ፣ ሐሜተኞች፣ ራሳቸውን የማይገዙ፣ ጨካኞች፣ መልካም የሆነውን የማይወዱ፣ ከዳተኞች፣ ችኩሎች፣ በትዕቢት የተነፉ፣ ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ ይሆናሉ፤ የአምልኮት መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ክደዋል፤ ከእነዚህ ደግሞ ራቅ።››** ይላል። 2ጢሞ.3÷2- 6

ሳያመልኩ አገልግሎት ውስጥ መኖር ምን ያስከትላል? ለራሱ መልስ የሌለው አገልግሎት ማለት፤ በእውነት እግዚአብሔርን ተገናኝቻለሁ? ከልዑል አምላክ ጋር በመንፈሳዊ በረከት ውስጥ ነኝ? አገልግሎቴ ለሌላው በረከት እየሆነ ነው? የተቸገረውንና የተጨነቀውን ሁሉ እውነተኛ የሆነ መንፈሳዊ ተስፋ፤ እግዚአብሔር በእኔ በኩል

ጌታችን መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፤ በጌቴሴማኒ ላይ በሚጸልይበት ጊዜ ደቀመዛሙርቱ የአገልግሎቱ ጊዜ የናፈቃቸው ቢሆንም፤ ደክመው ተኝተው ነበር። ለጸሎትና ለአምልኮ ጊዜና ቦታም፤ አልሰጡም ነበር። እርሱ ጸልዮ ሲመለስ፤ አሁንም ተኝተዋል። ቀስቅሶዋቸው ይሄዳል። እንደገና ጸልዮ ሲመለስ፤ አሁንም ተኝተዋል። ከዚያ በኋላ ምን አላቸው? **‹‹ከእኔ ጋር አንድ ሰዓት እንኳን መጸለይ አቃታችሁን?›› አላቸው። ማር. 14÷37 ለጸሎት ጊዜ አለመስጠት ራእይን ያጠፋል።**

ራእይ፤ በጨለመብን ወቅት ያበራልናል። ከጭንቀትና ከክፉ መንፈስ ጋር እንዳናድር ጌታችን መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ከእኛ ጋር አደር እንበለው። ራእይ የሌለው ትውልድ ዘመኑ እንደ ዔሊ ዘመን መልስ የሌለው ድካም ይሆንበታል።

## 8.4 ሰማያዊ አምልኮትና የቅድስና ምስጋና፤

አምልኮትን መፈጸም የሚችሉት ቅዱሳን መላእክትና የሰው ልጆች ናቸው። ቅዱሳን መላእክት ቅዱስ፤ ቅዱስ፣ ቅዱስ እግዚአብሔር የሠራዊት ጌታ እያሉ ያመሰግኑታል። እያመሰገኑም ለክብሩ ይሰግዳሉ። እያመሰገኑ፤ ከእሱ መንፈሳዊ ኃይል ዕለት፤ ዕለት ያገኛሉ።

ሰዎችም እንደ መላእክት ቅዱስ፤ ቅዱስ፣ ቅዱስ እግዚአብሔር የሠራዊት ጌታ፣ ሃሌሉያ እያሉ እያመሰገኑ፤ ለአብ እንሰግዳለን፤ ለወልድ እንሰግዳለን፤ ለመንፈስ ቅዱስ እንሰግዳለን፤ እያሉ በሚሰግዱበት ጊዜ ከስሙ በረከት ስለሚካፈሉ፤ ቅዱስ የመሆን ዕድል ያገኛሉ። ‹‹እኔ **ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ . . . የጠራችሁ ቅዱስ እንደሆነ እናንተም ደግሞ በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ።››** በማለት በ1ኛ ጴጥ.1÷15 ላይ ያስተላለፈው ቃል፤ ሕያው የሆነ ስጦታውን ያሳያል።





ቅዱስ መሆን የሚመነጨው፤ ስለ ቅዱስ እግዚአብሔር ያለን የአምልኮት ክብር እየጨመረ ሲመጣ ነው። በዚህ መካከል ደግሞ ራእይ አለ ማለት ነው። ራእይ የሌለው አገልግሎት በሰዎች ሕይወት ውስጥ ቦታም፣ ሥፍራም፣ ተስፋም የለውም።

ራእይ የሚከሰተው በእግዚአብሔር ምሪት ብቻ ነው። እግዚአብሔር እንዲመራ ማድረግ ነው። በዚህ ሁኔታ ብዙዎች አባቶች፣ ነብያትና ቅዱሳን ተጠቅመውበታል።

ራእይ እግዚአብሔር አምላክ ራሱን ገልጦ የሚናገርበት ኃይል ነው። ይህም፤ እንደ ዘመኑ ሁኔታና እንደየ ትውልዱ ጠባይ ይለያያል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደምንመለከተው፤ በአንደኛ ሳሙኤል ላይ፤ ሐና ለራእይ ትጸልይ ነበር። እግዚአብሔር እንዲሰማት፤ እንዲወዳትና እንዲያከብራት ትለምን ነበር። ባሏ ቢወዳትም፤ የልጅ ፍሬ አልነበራትም። ስለዚህ በአምልኮት ጊዜ ወደ ቤተ መቅደስ በመሄድ ለእግዚአብሔር ተንበርክካ ጸለየች።

እግዚአብሔር በዔሊ በኩል ጸሎቷን ሰማት። የራእይ ባለቤት የሆነችው ሐና፤ ራእይዋ የተገለጠው በችግሯ ወስጥ ሲሆን፤ የእሷ ትልቁ ራእይ ልጅ ማግኘት ስለነበር፤ በእግዚአብሔር ፊት ባደረገችው አምልኮት መልስ አግኝታ፤ ልጅ መውለድ ቻለች።

ልጁንም፤ ለእግዚአብሔር ቤት ለዘለዓለም ሰጥቼዋለሁ! ስትል ቃል ገባች። ። የጸሎቷ ጊዜና ሰዓት ወደ ፍጻሜ ሲመጣ ልጅ አገኘች፤ ሳሙኤል ተወለደ።

ዔሊ በዘመኑ ከነበሩ አባቶች አንዱና ትልቁ፤ ከልዑል እግዚአብሔር አምላክ ሞገስን የተቀበለ፤ በበረከት ተስፋ ውስጥ እንዲቆም በቤቱ የማምለክና የማገልገል ዕድል ያገኘ፤ በእስራኤልም ሕይወት ውስጥ የመሪነቱን ሥፍራ ይዞ፤ ፍትህ ሳይዛባ የሕብረተሰቡ መንፈሳዊ አገልግሎት ሳይደበዝዝ፤ እንዲኖር እግዚአብሔር አምላክ ያስቀመጠው ሊቀ ካህን ነበር።

ሕዝበ እሥራኤል «**የእግዚአብሔርን ቁርባን ይንቁ ነበር**፡፡» በምን ዓይነት ወቅትና ሰዓት ላይ ነው የቆምነው? የሰዎች መንፈሳዊ ቅድስና መቶ በመቶ የቀዘቀዘበትና የእግዚአብሔር መንገድ የተናቀበት፣ በእምነት የዋለልንበት፤ ከሕይወት ጎዳና አንፃር ሲታይ ደግሞ፤ በሰላማዊ መንገድ በአምላክ ተስፋና ኃይል የመመራት ጸጋና ሞገስ ጠፍቶ፤ በፍርሃትና በጭንቀት የታሰርንበት ሰዓት ላይ ቆመናል፡፡

**ሰዎችም የእግዚአብሔርን ቁርባን ይንቁ ነበር!** በቅድሚያ እነዚያ ሰዎች የሚያዩት፤ በደጁና በመለኮት የአገልግሎት ምሪት ውስጥ ያሉትን አገልጋዮችን ነበርና፡፡ የዔሊ ልጆች የእግዚአብሔርን ቁርባን አስንቀዋል፤ የቤተ-እግዚአብሔርን ክብር አዋርደዋል፤ በሕዝቡም ዘንድ መሰናክል በመሆን የእግዚአብሔርን ስም አሰድበዋል፡፡

በዓለም ውስጥ ብዙ ተረትና ምሳሌዎች የሚመነጩት ከንቀት ጋር በተያያዘ፤ በመንፈሳዊ በረከት ላይ ቆመዋል ከሚባሉ ሰዎች አካባቢ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ፤ በሕይወታችን ውስጥ በንቀት ከምናያቸው ክፍል ውስጥ አንደኛው፤ የመንፈሳዊውን አገልግሎትና ሥፍራን ነው፡፡

ከትምህርትና ከዕውቀት አንጻር ሲታይ ግን፤ ቅድሚያ የምንሰጠው ለሥጋዊ ሥልጣኔና ጥበብ እንጂ፤ ለመንፈሳዊ ጉዳይ አይደለም፡፡ እናቶችና አባቶች ከእግዚአብሔር አምላክ ቁርባን ሳይገናኙ ያልፋሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ቅዱስ ቁርባን መውሰድን፤ እንደ ዘመን መጨረሻ አድርገው ይመለከቱታል፡፡ ሳታረጁ ቅዱስ ቁርባን ከወሰዳችሁ ዓይናችሁ ይጠፋል፤ የማያዛልቅ ጸሎት ለቅሰፈት፣ እየተባሉ የሚተረቱት ተረቶች፤ በመንፈሳዊ ሕይወት ላይ ለሚኖረን ጥንካሬ ለብዙዎች እንቅፋት ሲሆን ኖሯል፡፡ በመሆኑም፤ ሲጸልዩና ሲቆርቡ የሚታዩት፤ ለትውልድ በረከትን ለማምጣት ሳይሆን፤ አንዳንዴም ለወግና ለልማድ ሆኖ ይታያል፡፡





ሃይማኖትን ከባሕል ጋር አዳብለው ክፉ ነሮችን በሃይማኖት ውስጥ አስገብተው ሲወቅሱና ሲተቹ፤ እንደበቶቻቸው ላይ ትንሽ እንኳን ማሰሪያ አያበጁለትም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ፤ **ሰዎችም የእግዚአብሔርን ቁርባን ይንቁ ነበር**፡፡ ያለው ለዚህ ነው፡፡

## 8.6 <u>የድፍረት አገልግሎት</u>

ራእይ የሌለው አገልግሎት ትውልድ ሲበላሽ የሚያይበት፤ ወይም የሚያውቅበት መንገድ የለውም፡፡ እያገለገልን ደፋር ነን፤ ሥጋዊ ድፍረት ነው ያለን፤ መንፈሳዊ ሆኖ ከመሥራት ይልቅ፤ በሥጋ ድፍረት ነው የምናገለግለው፡፡

ሥጋዊ ድፍረት የሚያመጣቸውን ችግሮች አስቀድመን ለመገንዘብ የምንችልበት አቅም የሚገኘው፤ በአምልኮት ውስጥ የእግዚአብሔርን ምሪት ስንፈልግ ነው፡፡

ከዚህ ውጭ ከሆነ ግን፤ በራሳችን ምሪት እና ድፍረት ማገልገል ስንጀምር፤ በተመልካች ዘንድ ብዙ እንቅፋቶች ከመደቀናቸውም በላይ፤ የሌሎችንም መንፈሳዊ ሞራል በማዳከሚያ መልኩ ሰይጣን ከመጠቀሙም በላይ፤ በመንፈሳዊ ሕይወት ውስጥ ታሪካዊ ድክመት የተገለጠ ይሆናል፡፡

**መጽሐፈ ሳሙኤል ምዕራፍ ሁለት ቁጥር ሃያ ሁለት ላይ** እንደተጠቀሰው፤ የዔሊ ልጆች «**በመገናኛውም ድንኳን ደጅ ከሚያገለግሉት ሴቶች ጋር እንደተኙ ተሰማ**፡፡» ይላል፡፡

ይህ እንግዲህ ከድፍርት አገልግሎት አንዱ ነው፡፡ በድፍረት እያገለገሉ ራእይ የለም፡፡ በመካከል ደግሞ፤ የድፍረት ኃይል አባት የሆነው ዲያብሎስ፤ አጥፊ የሆኑ ረዳቶቹን አገኘ፡፡ በዚህም፤ አገልግሎቱ ሙሉ በሙሉ ወደ ድፍረት አገልግሎት ተለወጠ፡፡

ያ ትውልድ በእግዚአብሔር አምላክ ታሪክ ውስጥ የወደቀበትና ያዘነበት፤ ሽማግሌዎች በውርደት የተለዩበት፤ መንፈሳዊ አምባዎች

በከፋ ጠላት የተያዙበት፣ ብዙ በረከቶችንና ክብሮችን ያጡበት፣ በአጠቃላይ ታሪካቸው የቀዘቀዙበትና የወደሙበት ዘመን ሆነ።

የመንፈሳዊ ታሪክ ጀግንነት መቶ በመቶ ከእስራኤል የቃልኪዳኑ ኃይል የተቋረጠበት፣ የአረማውያን መዘባበቻና መቀለጃ የሆኑበት ምክንያት፣ በዚህ የድፍረት አገልግሎት የተነሣ ነው።

ከውድቀት በፊት ድፍረት እየጨመረ ይመጣል። ከዚያ በኋላ ውድቀት ይከተላል። ወይም፣ ከሞት በፊት የዲያብሎስ ክፉ ሥራ እየበረታ ይመጣል፣ ከዚያ በኋላ ሞት ይከተላል።

ከመንፈሳዊ ተስፋ ይልቅ፣ ራእዮቹ ቆመውና ሰማያዊ መልዕክቶች ተቋርጠው ባለበት ሕሊና ውስጥ፣ የሚከሰተው ነገር፣ ከእስራኤል ታሪክ እንጻር ስናይ፣ እጅግ በጣም አሳዛኝ ጉዳት እንደገጠማቸው፣ ታቦተ ጽዮንን እንዳስማረኩና የእግዚአብሔር ሕዝብ በጠላት እንደተመታ ስንረዳ፣ ላመንፈሳዊ ሕይወትና ለቅድስና የምንሰጠው ቦታ፣ እንዴት ታላቅ መሆን እንዳለበት እንገነዘባለን።

እኛም፣ በጣም ደፋሮች ነን። አንድ ወቅት ላይ የሕዝቡን ነጻነት ከመንፈሳዊ በረከት በባዶ <u>ድፍረት</u> አላቀን፣ በዓለማዊ ነጻነት እንተካለን ብለን፣ተነሣን። እግዚአብሔር የለም የሚለውንም ትምህርት እንደ አዲስ ራእይ ይዘን በመዝመት፣ ትውልዱን ሁሉ ጎዳን።

የቤተመቅደሱን መንፈሳዊ ጉዞ ዘጋን፣ ሰደብን፣ አዋረድን፣ እንደ ካህን እንደ ቄስ እያልን ቀለድን፣ ብዙ መንገዶችን ሄድን፣ ትልልቅ ሥጋዊ ትምህርት ቤቶችን አፈራን።

የድፍረቱ ዓላማ፣ በመንፈሳዊ መርሆ ላይ የቆመውን ትውልድ አእምሮ መንካት ስለነበር፣ ተሳክቶም የተነካ ትውልድ ሆነን። የቤተክርስቲያንን መውጫና መግቢያ በሮችንም ዘጋን፣ በዚህ መሄድ የለባቸውም አልን፣ የተራማጆች መንገድ ብለን ሰየምነው።

አልፎ ተርፎም፣ በቤተክርስቲያን ቅጥር ውስጥ የሚገኙ የመቃብር ሥፍራዎችን፣ <u>በተለይ ለአብዮታውያን</u> የተባለ ቦታ





በማዘጋጀት ሰየን። <u>አምልኮት የሌለበት አገልግሎትና የድፍረት ዘመን</u> እንዲህ ነው። የእግዚአብሔር ራእይ የሌለው ትውልድ፣ በመንፈሳዊውም ሆነ፣ በሥጋዊው አኗኗሩ አገልግሎቶቹ ሁሉ፣ በድፍረት የተሞሉ ናቸው። ‹‹አትሳቱ እግዚአብሔር አይዘበትበትም። ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳል።›› ገላትያ 6÷7

## 8.7 <u>የእግዚአብሔርን ቃል የማይሰሙበት አገልግሎት</u>

ዛሬ እኛ ሲቸግረን ነው የእግዚአብሔርን ቃል የምንሰማው። ቤቱ ሞልቶ፣ የኢኮኖሚ አቅሙ ተሻሽሎ የተደላደለ ኑሮ ለሚኖረውና ለሚመራው ሰው የእግዚአብሔርን ቃል ብትነግሩት፣ ብዙም የሚሰማችሁ አይደለም።

ቃሉ እንዲህ ይላል፣ ‹‹ዔሊም እጅግ አረጀ፣ ልጆቹም በእስራኤል ሁሉ ላይ ያደረጉትን ሁሉ፣ በመገናኛውም ድንኳን ደጅ ከሚያገለግሉት ሴቶች ጋር እንደ ተኙ ሰማ። እርሱም አላቸው፦ ስለ ክፉ ሥራችሁ ከዚህ ሕዝብ ሁሉ ሰምቻለሁና ስለ ምን እንዲህ ያለ ነገር ታደርጋላችሁ? ልጆቼ ሆይ፣ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ኃጢአተኛ በማድረጋችሁ ስለ እናንተ የደረሰኝ ወሬ መልካም አይደለም ይህ አይሆንም። ሰውስ ሰውን ቢበድል እግዚአብሔር ይፈርድበታል፣ ሰው ግን እግዚአብሔርን ቢበድል ስለእርሱ የሚለምን ማን ነው? ›› አላቸው። ሳሙ. 2÷25

የራእይ ፍላጎት ባለው ልብ ውስጥ መመለስ እና በአምልኮት የሚገለጥ ተስፋ፣ ከእግዚአብሔር የመጠበቁ ጊዜ ሁኔታ በፊት ቀረ። አሁን ዔሊ ሉሉ.. አለ። መጮሕ ጀመረ። ‹‹ሰው ሰውን ቢበድል እግዚአብሔር ይፈርድበታል፣ ሰው ግን እግዚአብሔርን ቢበድል ስለ እርሱ ማን ይለምናል? እነርሱ ግን እግዚአብሔር ሊገድላቸው ወድዷልና የአባታቸውን ቃል አልሰሙም።

ሁለተኛው፤ **<u>ፊንሐስ</u>** ማለት ደግሞ <u>**ሃፍረተቢስ**</u> ማለት ነው። የስም ስያሜያቸው የዘመኑን የሕብረተሰብ ጠባይ የተከተለ ከመሆኑም በላይ፤ በሕይወታቸውም ሲገለጥ፤ የስማቸውን ገጸ ባሕርይ በተግባር እንደኖሩበት እንረዳለን።

በመንፈሳዊ ጉዞ ውስጥ የስም አወጣጥ ገጽታ፤ ለአምልኮት ክብር ከሚሰጠውና ክብር ከማይሰጠው ወገን መካከል፤ አንዱ የመለያ አካል ነው። በእኛም አገር ኑሮው ሲከብደን፤ ‹‹ከበደ››፣ ረዳትና ኃይል ስንፈልግ፤ ‹‹መኩታ››፣ ዘመኑ ደስ ሲለን፤ ‹‹ደስታ›› ሰላም ስናጣ ደግሞ፤ ‹‹አሸብር›› እንላለን። ልክ በዚሁ ዓይነት በኤሊ ዘመን የነበሩት የዔሊ ልጆች ዔሊ የነበረበትን ወቅትና ኑሮ ለመግለጽ ሲፈልግ፤ አፍኒን (ጠበኛ) ፊንሃስ (ሃፍረተ-ቢስ) እንዳላቸው እናስተውላለን።

አሳዛኙ ገጽታ፤ የዔሊ ልጆች ይህንን ስም ይዘው፤ የእግዚአብሔር ቤት ካህን መሆናቸው ነው። ገና ከማለዳ ስማቸውን የተከተለ የክፉ መንፈስ ጥቃት የሕይወታቸው ፍጻሜ፤ አሳዛኝ እንዲሆን አድርጎታል።

በእኛ አገር ለልጅ ስም ሲወጣ፤ በአብዛኛው ወቅትና ጊዜን ተመልክቶ ነው። የመከራ ጊዜዎቻችንና ገጠመኞችንን ተንተርሰን፤ ለልጆቻችን የምናወጣቸው ስሞች፤ ዲያብሎስ የሚከተላቸው ይሆናሉ።

ተጸልዮበት፤ ልጅ ስለሰጣቸው እግዚአብሔርን አመስግነው፤ በአምልኮት ውስጥ የቅድስና ስሞችን ፈልገው አይደለም የሚያወጡት። በሚያወጡትም ስም፤ ርኩሳን መናፍስት የስሞቻችንን ጠባይ ተከትለው፤ በሕይወታቸው ውስጥ ገብተዋል። እንኳን አስጨናቂ፣ ዳምጠው፣ አሸብር፣ ከበደ ወዘተ... ተብለው ቀርቶ፤ ‹‹አብርሃም›› የተባለው ላይ እንኳን፤ ውጊያው ከፍተኛ ነው።

የቃየን ዘሮች በእግዚአብሔር ስም ፈጽሞ አልተጠሩም እንደደዛሬው ስም አውጪ ቤተሰቦች በላቸው፣ እርገጤ፣ ሸንቁጤ፣ ቅጣው፣ ዳምጠው፣ ዘርጋው፣ ከልክሌ፣ ደቁሴ፣ አምታታው፣ አርምዴ





ወዘተ... ለዘመናት አምላክ የማይጠራበት ስሞቻችን ዓይነት የቃየንም ዘር ስሞች እንዲሁ ነበሩ።

ዛሬ በክርስትና ስም መጠራት ፈጽሞ የተረሳ ጉዳይ ሆኗል። የክርስትና ስም የሚታወሰው ሰው ሲሞት ለፍታት ብቻ እየሆነ መጥቶአል። ብዙ ጊዜም እየተረሳ ከሞተ በኋላ አዲስ የክርስትና ስም ይወጣለታል። ይህን ያህል የቀዘቀዝን፣ የእምነትን ኃይልና ዋጋን ያልተረዳን ሆነናል። ዘፍ. 4÷25 ‹‹**አዳም ደግሞ ሚስቱን አወቀ፤ ወንድ ልጅም ወለደች። ስሙን፦ ቃየን በገደለው በአቤል ፋንታ እግዚአብሔር ሌላ ዘር ተክቶልኛል ስትል ሴት አለችው። ለሴት ደግሞ ወንድ ልጅ ተወለደለት ስሙን፦ ሔኖስ አለው፤ በዚያን ጊዜም በእግዚአብሔር ስም መጠራት ተጀመረ።** ››

ከዚህ ቃል የምንማረው ለልጆቻችን ስም ስናወጣ በጸሎትና በመንፈሳዊ አምልኮት የተጠናከረ፤ ከእግዚአብሔር ክብር ጋር የተያያዘ መሆን እንደሚገባው በቅድሚያ ልናስብበት ይገባል።

## 8.10 የተሸነፈ ትውልድ፤

አፍኒንና ፊንሃስ ሜዳ ላይ ቀርተዋል፤ ዔሊም አንገቱ ተሰብሮ መንገድ ዳር ሞቷል። ይህ ከሆነ በኋላ፤ የፊንሃስ ሚስት በመጥፎው ዘመን መውለድ ስትጀምር፤ ተንበርክካ ወለደች። የልጁንም ስም፤ ‹‹ኢካቦድ›› አለችው። ኢካቦድ ማለት፤ የእግዚአብሔር ክብር ከእግዚአብሔር ሕዝብ ለቀቀ ማለት ነው። እዚህ ላይ፤ ውርደቱ በአካል ተረጋገጠ።

ከዘርህ የሚቀር ቢኖር ዓይንህን ያፈዘዋል፤ ሰለተባለ፤ ያ የክፋትና የእርግማን ስም ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተሸጋገረ መጥቶ፤ የእግዚአብሔር ክብር የለቀቀበት፤ የሐዘን፣ የሥቃይና የሽንፈት ትውልድ ላይ ደረሰ።

ዛሬ በእኛ ኑሮ በዘመናችንና በመንፈሳዊ ጉዞአችን ውስጥ ያሉትን አንዳንድ ሁኔታዎች ስንመለከት፤ ከማሳደድ፣ ከመንቀል፣ ከወሬ፤ ከክፋት፤ ከምቀኝነት ወዘተ... ጋር የተያያዙ፤ በርካታ ከእግዚአብሔር ክብር የራቁ ምሳሌዎችን መጥቀስ እንችላለን። ምክንያቱም፤ ለአምልኮት ቦታና ጊዜ የለንም።

ከዚህም በተጨማሪ፤ በዔሊ አምልኮት ማጣት ምክንያት የነበረው ተስፋ መቁረጥ፤ ዛሬም አብሮን አለ። ዔሊ አርባ ዓመት ሙሉ በውጣ ውረድ የኖረበት ሕይወት፤ ጠበኛና ሃፍረተ ቢስ ልጆችን ሲያስገኝለት እንኳን፤ ሊነቃ አልቻለም።

ስለዚህ ቢወልድ፤ አፍኒን፣ ፊንሃስ፣ ኢካቦድ! አባቶች ያቆዩለትን በረከት፣ አደራና ክብር፤ መጠበቅ ያልቻለ ትውልድ ተፈጠረ።

በአመዛኙ እኛም ልቦናችን ከአምላካችን ስለራቀ፤ ለእግዚአብሔር የተሰጡ ልጆች የሉንም። ለአዳል ሞቲ፣ ለወሰን ገፈ፣ ለጠቋር አባ ቡሌ፣ ለዛር አጋንንት፤ ወዘተ... ተስለን ስለወለድን፤ የእኛና የልጆቻችን ዕድል፤ የመከራ ሆነ።





የከፋ ችግር፣ ሐዘን፣ በሽታ፣ ስደት መታሰር፣ መገረፍ፣ መራብ፣ ወዘተ... የተለመዱና ቋሚ የኑሯችን መለያ ምልክቶች ሆኑ። በዛርና በውቃቢ መንፈስ የተለከፈ ማሕጸን፤ የሚያፈራው ደግሞ፤ ከእግዚአብሔር ክብር የራቀ ትውልድን፤ ኢካቦድን ነው።

‹‹ገለባን ትፀንሳላችሁ፤ እብቅንም ትወልዳላችሁ፤ እስትንፋችሁ የምትበላችሁ እሳት ናት።›› ት/ኢሳ. 33÷11

### የዔሊ፣ የአፍኒንና የፊንሐስ፤ የኢካቦድ ዘመን፤ አጠቃላይ መገለጫዎቹ፤

- ክብር የራቀውና የእግዚአብሔርን ታቦት ያስማረከ፤
- ታሪክ የወቀሰው አሳፋሪ ዘመን፤
- መሪና ተመሪ ያጣ (የተበተነ)፤ አባት የሌለውና ባዶውን የቀረ፤ መግቢያና መውጫው የጠፋው፣ ሰላም ያጣ ትውልድ፤
- ጠላት የሳቀበትና ያቃለለው፤ መተረቻና መዘባበቻ የሆነ፤
- የእርግማን ኃይል የገዛው፤
- ፍርሃት የተጠናወተውና የበረገገ ዘመን ነው።

### ቤተ-እግዚአብሔራችንን በቅድስና አለማገልገል፤

ቤተ-እግዚአብሔርን ከዓለም አንዛር ልዩ የሚያደርገው፤ የልብ፣ የአእምሮ፣ የሕሊናና የነፍስ የቅድስና ኃይል መኖሪያና መገለጫ በመሆኑ ነው።

እንዲሁም የእግዚአብሔር ተስፋና ራእይ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዳይቋረጥ፤ ሰውና እግዚአብሔር የሚገናኙበት፤ ኃጢአትና የዲያብሎስ ሥራ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚደመሰስበት፤ የአምላክ ምሕረትና ቸርነት የሚገለጥበት፣ በረከትና ሰላም፣ ፍቅርና ሞገስ፤ በእምነት የሰው ልጅ የሚጎናጸፍበት ቅዱስ ሥፍራ፤የአምላክ ማደሪያ ቤተ-እግዚአብሔር ነው።

ከዚህ በተጨማሪ፤ የእግዚአብሔር ዳኝነት በመንፈሳዊውም፤ በሥጋዊውም መንገድ ላይ የሚታይበትና ሚዛናዊ ፍርድ ባለበት

## 8.10 የተሸነፈ ትውልድ፤

አፍኒንና ፊንሃስ ሜዳ ላይ ቀርተዋል፤ ዔሊም አንገቱ ተሰብሮ መንገድ ዳር ሞቷል። ይህ ከሆነ በኋላ፤ የፊንሃስ ሚስት በመጥፎው ዘመን መውለድ ስትጀምር፤ ተንበርክካ ወለደች። የልጁንም ስም፤ <u>‹‹ኢካቦድ››</u> አለችው። ኢካቦድ ማለት፤ <u>የእግዚአብሔር ክብር ከእግዚአብሔር ሕዝብ ለቀቀ</u> ማለት ነው። እዚህ ላይ፤ ውርደቱ በአካል ተረጋገጠ።

<u>ከዘርህ የሚቀር ቢኖር ዓይንህን ያፈዘዋል፤</u> ስለተባለ፤ ያ የክፋትና የእርግማን ስም ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተሸጋገረ መጥቶ፤ የእግዚአብሔር ክብር የለቀቀበት፤ የሐዘን፣ የሥቃይና የሽንፈት ትውልድ ላይ ደረሰ።

ዛሬ በእኛ ኑሮ በዘመናችንና በመንፈሳዊ ጉዞአችን ውስጥ ያሉትን አንዳንድ ሁኔታዎች ስንመለከት፤ ከማሳደድ፣ ከመንቀል፤ ከወሬ፤ ከክፋት፤ ከምቀኝነት ወዘተ... ጋር የተያያዙ፤ በርካታ <u>ከእግዚአብሔር ክብር የራቁ</u> ምሳሌዎችን መጥቀስ እንችላለን። ምክንያቱም፤ ለአምልኮት በታና ጊዜ የለንም።

ከዚህም በተጨማሪ፤ በዔሊ አምልኮት ማጣት ምክንያት የነበረው ተስፋ መቁረጥ፤ ዛሬም አብሮን አለ። ዔሊ አርባ ዓመት ሙሉ በውጣ ውረድ የኖረበት ሕይወት፤ ጠበኛና ሃፍረተ ቢስ ልጆችን ሲያስገኝለት እንኳን፤ ሊነቃ አልቻለም።

ስለዚህ ቢወልድ፤ አፍኒን፣ ፊንሃስ፣ ኢካቦድ! አባቶች ያቆዩለትን በረከት፣ አደራና ክብር፤ መጠበቅ ያልቻለ ትውልድ ተፈጠረ።

በአመዛኙ እኛም ልቦናችን ከአምላካችን ስለራቀ፤ ለእግዚአብሔር የተሰጡ ልጆች የሉንም። ለአዳል ሞቲ፣ ለወሰን ገፌ፣ ለጠቋር አባ ቡሌ፣ ለዛር አጋንንት፤ ወዘተ... ተስለን ስለወለድን፤ የእኛና የልጆቻችን ዕድል፤ <u>የመከራ</u> ሆነ።





የክፋ ችግር፣ ሐዘን፣ በሽታ፣ ስደት መታሰር፣ መገረፍ፣ መራብ፣ ወዘተ... የተለመዱና ቋሚ የኑሯችን መለያ ምልክቶች ሆኑ። በዛርና በውቃቢ መንፈስ የተለከፈ ማሕጸን፤ የሚያፈራው ደግሞ፤ <u>ከእግዚአብሔር ክብር የራቀ ትውልድን፤ ኢካቦድን ነው።</u>

**‹‹ገለባን ትፀንሳላችሁ፤ እብቅንም ትወልዳላችሁ፤ እስትንፋችሁ የምትበላችሁ እሳት ናት።›› ት/ኢሳ. 33÷11**

### <u>የዔሊ፣ የአፍኒንና የፊንሐስ፤ የኢካቦድ ዘመን፤</u>
### <u>አጠቃላይ መገለጫዎቹ፤</u>

- ክብር የራቀውና የእግዚአብሔርን ታቦት ያስማረከ፤
- ታሪክ የወቀሰው አሳፋሪ ዘመን፤
- መሪና ተመሪ ያጣ (የተበተነ)፤ አባት የሌለውና ባዶውን የቀረ፤ መግቢያና መውጫው የጠፋው፣ ሰላም ያጣ ትውልድ፤
- ጠላት የሳቀበትና ያቃለለው፤ መተረቻና መዘባበቻ የሆነ፤
- የእርግማን ኃይል የገዛው፤
- ፍርሃት የተጠናወተውና የበረገገ ዘመን ነው።

<u>ቤተ-እግዚአብሔራችንን በቅድስና አለማገልገል</u>፤

ቤተ-እግዚአብሔርን ከዓለም አንፃር ልዩ የሚያደርገው፤ የልብ፣ የአእምሮ፣ የሕሊናና የነፍስ የቅድስና ኃይል መኖሪያና መገለጫ በመሆኑ ነው።

እንዲሁም የእግዚአብሔር ተስፋና ራእይ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዳይቋረጥ፤ ሰውና እግዚአብሔር የሚገናኙበት፤ ኃጢአትና የዲያብሎስ ሥራ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚደመሰስበት፤ የአምላክ ምሕረትና ቸርነት የሚገለጥበት፣ በረከትና ሰላም፣ ፍቅርና ሞገስ፤ በእምነት የሰው ልጅ የሚጎናጸፍበት <u>ቅዱስ ሥፍራ፤የአምላክ ማደሪያ ቤተ-እግዚአብሔር ነው።</u>

ከዚህ በተጨማሪ፤ የእግዚአብሔር ዳኝነት በመንፈሳዊውም፤ በሥጋዊውም መንገድ ላይ የሚታይበትና ሚዛናዊ ፍርድ ባለበት

ዲያብሎስ ይደሰታል፡፡ በአጠቃላይ፤ እነዚህ ድክመቶች ባሉበት ወደ ሕዝብ ልንሄድ ቀርቶ፤ ራሳችንም ከዚህ ልማዳዊ አገልግሎት ወጥተን፤ ወደ ቅድስናው አምልኮት የምንደርስበት ኃይልና ጉልበት አጥተናል፡፡ ቤተክርስቲያን ከአምላካችን የተቀበለችው አደራ ግን፤ **‹‹ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው፡- ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ፡፡ እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፣ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ፡፡››** ማቴ 28÷18-20 የሚል ነው፡፡

## ማጠቃለያ

ዛሬ የገድለ-ዲያብሎስ የዝና ታሪክ፣ የኃጢአትና የሞት ዜና መረጃ በበዛበት ዓለም ውስጥ እንገኛለን፡፡ ኃጢአት፤ ለዚህ ዘመን ሰው የመጀመሪያው እውቀትና የሥነ-ምግባሩ መግለጫ በመሆን፤ ጸሎት ጽድቅንና እውነትን የባርነት መንገድ አድርጎ እንዲያይ፤ የትውልዱ የውድቀት ጉዳይ ፈጻሚ የመሆን ዕጣ ድርሻውን ከዲያብሎስ ተምሯል፡፡

**‹‹በጎ እያደረጋችሁ፣ የማያውቁትን ሞኞች ዝም ታሰኙ ዘንድ እንዲህ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነውና፤ አርነት ወጥታችሁ እንደ እግዚአብሔር ባሪያዎች ሁኑ እንጂ ያ አርነት ለክፋት መሸፈኛ እንዲሆን አታድርጉ፡፡››** 1ጴጥ 2÷15-16

ክፉ መናፍስት፤ በሕይወታችንና በኑሯችን ውስጥ፤ ሥፍራና ቦታ አግኝተው፤ በውድቀት አዙሪት ውስጥ እንድንኖር ሊያደርጉ የቻሉበት አንዱና ዓብይ ምክንያት፤ ለአምላካችን ለእግዚአብሔር የቅድስና አምልኮትና ጸሎት ባለማድረጋችን ነው፡፡





ከዲያብሎስ መሠረታዊ ሥልት አንዱ፤ በዓለማዊው መድረኮች ላይ ለመንፈሳዊ ሕይወት ቦታ እንዳይሰጥ፤ በተለይም ጸሎት ወደ እግዚአብሔር እንዳይደረግ ማዘናጋት ነው፡፡

ጸሎት አለማድረግ ደግሞ፤ ከእግዚአብሔር የሚያለያየን ዋነኛ መንገድ ነው፡፡ ዛሬ በዚህ ጎዳና ላይ እኛም እየተጓዝንበት እንገኛለን፡፡ ከአምላክህ ጋር ከተለያየህ ደግሞ፤ የምታዳብረው ጠባይ፤ ክፋትን፣ ተንኮልን፣ ፊዘኝነትና ደንታ ቢስነትን ወዘተ... ነው፡፡

በዚህ መንገድ ከተጓዝን ደግሞ፤ ጸሎት የለም፡፡ ምናልባት የምንሰማውና የምናየው የአንድና የሁለት ደቂቃ የሕሊና ጸሎት የሚባለውን ነው፡፡ የሚገርመው ግን፤ ይህ የሕሊና ጸሎት ለማን እንደሆነ፣ ምን ተብሎ እንደተጸለየና ማን እንደሰማው አለመታወቁ ነው፡፡

እንደዚህ ዓይነቱ ጸሎት፤ ዘመናዊው ሰው ምንጊዜም አቀጣጫውን ሲለውጥ፣ እምነቱን ሲጥል፣ የማንነት ጉዳዩን ከመናቅም በላይ፤ አዲስ ነገርና የፈጠራ ሃሳብ መሞከሪያ ሲሆን፤ እራሱን እያዘናጋ በሕይወት ተምሳሌቱና ከጊዜው እይታ ጋር ሲወዳደር፤ ለየግል ፍላጎቱ ከሥራ ጋር ሲባዝንና ሲሯሯጥ፤ በመሐል ሃይማኖቱንና እምነቱን በመዘንጋት፤ ለከባድ መቅሰፍት እንዲጋለጥ የሚያደርግ ነው፡፡

ጸሎት፤ ከእውነተኛ አምልኮ ጋር የሚሄደው፤ ‹‹**አባታችን ሆይ! በሰማያት የምትኖር ስምህ ይቀደስ መንግስትህ ትምጣ** ›› ብሎ የሚጀመር ሲሆን ነው፡፡ ታዲያ ኃጢአት የኃፍረተ-ቢስነት፣ የአመፃ፣ የርኩሰትና የመቅሰፍት ቁጣ መግለጫ ሆኖ መቀመጡን መሰማት ብቻ ሳይሆን፤ በዓይናችን እያየነው፤ መንፈሳዊው ግብራችንና አመለካከታችን፤ ከክፉው ዓለም አመጸኞች የማይለይበት ሁኔታ ውስጥ መገኘቱ፤ ብዙ ጊዜ ይስተዋላል፡፡

## ተጨማሪ መረጃዎች፤

የመናፍስቱን የውጊያ ሥልቶችና ጥቃቶች፤ ለማወቅና ሕብረተሰባችንን ምን ያህል እንደጎዱት በግልጽ ለመገንዘብ፤

- በተአምረ ጽዮን ሰቂዲዮ፤‹‹ንቁ ›› በሚል ርዕሥ የተዘጋጀውና፤ ከቁጥር አንድ እስከ አስራ ስምንት ድረስ እንዲሁም ከዚያም በላይ ያሉትን መንፈሳዊ የቪ.ሲ.ዲ. ፊልሞች ደጋግሞ በመመልከት፤
- **www. Radio Abissiniya.Com**
  ከአሜሪካን አገር በአቢሲኒያ ሬድዮ ጣቢያ የሚሰራጨውንና ‹‹ የመምህር ግርማ ወንድሙ መልእክት ›› በሚለው ፕሮግራም ላይ የሚተላለፈውን ትምህርት በመከታተል፤ ስለ ክፉ መናፍስት ጥቃቶች የበለጠ መረዳት ይቻላል።

---

## ቀጣዩ መጽሐፍ

# በማለዳ መያ’ዝ ፤ ቅጽ - ፪

1. የእግዚአብሔር ተስፋና የሰው ልጅ ፈተናዎች፤
2. የእርግማን ዘር ምልክቶችና የወንዝ ዳር ልጆች፤

እንዲሁም

ሌሎች፤ በድምሩ ሰባት ምዕራፎችን አጠቃሎ

በመያዝ፤ በቀጣይነት ይወጣል።

---




የቅዱስ እስጢፋኖስ ዓመታዊ ክብረ በዓል ግንቦት 17 ቀን 2004 ዓ.ም




በቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን የሚካሄደው ጉባኤያችን

## ከመጽሐፉ የውስጥ ገጾች የተወሰደ...

**...... ለምድርና ለባሕር ወዮላቸው፤ ዲያብሎስ ጥቂት ዘመን እንዳለው አውቆ በታላቅ ቁጣ ወደ እናንተ ወርዶአልና፤ ራእይ 12፡12**

**ደጋ ላይ የወደቀው ሰይጣን፤** የሰዎችን የአናኗር፣ የባሕል፣ የወግና የልማድ ወዘተ... የማህበራዊ ኑሮ አካባቢያዊ መርሆችን መሠረት አድርጎ፤ እንደ ቀየውና እንደ የመንደሩ መጠሪያውን አገኘና፤ ዛር፣ ውቃቢ እየሆነ፤ እየተሾመ፤ እየተሸለመ፤ ሿሚና ሽላሚዎችን እያበጀ፤ አዳል ሞቲ፣ ወሰንገሬ፣ ጠቋር አባ ቡሌ፣ የአርሲዋ እመቤት፣ የታዬ ከራማ፣ አውሊያ፣ አፋ-ደመና፣ አፋ-ለገሆ፣ አፋ-አቡኮ፣ ሰይፉ ጨንገር፣ ራስ ሐጎስ፣ ግራኝ አባ ጉግሳ፣ ቡሎ ገርቢ ሳማ ቀልቢ፣ ሼህ አንበሶ፣ ሙጨ-ዘራጋ፣ ራሔሎ፣ አዮ ሞሚና፣ አርሜት፣ ድማማት፣ ሞሔት፣ ቦገና ወዘተ... እየተባለ፤ ሰይጣንነቱን በውስጡ ደብቆና የሰዎችን ስያሜ ይዞ፤ አገሩን ሁሉ እንደ ውኃ ሙላት አጥለቀለቀ።

**ፀሪሃ ላይ የወደቀው አጋንንት፤** በበኩሉ፤ ለሥራ እየተፈለገ፤ ለሙተት፣ ለሥልብና ለሚርት ገንዘብ ለመሰብሰብ፤ እየተሳበ ወደ ከተማ መጣ። « **ኃይል ሁነኝ፤ ስናገር የማሥፈራና የማስደነግጥ አድርገኝ!**» እየተባለ፤ ለግርማ ሞገስ እየተጠራ ባለፉት ዘመናት ብዙዎቻችን ቤት ገባ።

**የአየሩ አጋንንት፤** ጥሩ ራእይና ሕልም እንዳታይና እንዳይኖርህ፣ ጸሎትህ ወደ እግዚአብሔር ጸባዖት እንዳይሰማ በሰማይና በምድር መሃል በአየር ላይ ሆኖ ይከለክላል። ሕልምህን ነብር፣ አንበሳ፣ ዝንጀሮ፣ ዘንዶ፣ እባብ፣ አይጥ፣ እንቁራሪት፣ ጊንጥ፣ ጥልቅ ጉድጓድ ወይም ገደል፣ ድቅድቅ ጨለማ ወዘተ... በማድረግ፤ ትውልዱ ራእይ አልባ ሆነ።

**ከባሕር የወጣው የመናፍቁ መንፈስ** ደግሞ፤ መጽሐፍ ቅዱስ አስደፅና አሠልጥኖ፣ ምላሱን አስረዝሞ፣ አስተሳሰብን በቅራኔ መርዞ፣ የክህደትና የቤተክርስቲያንን ሥርዓተ አምልኮትን እየተሳደበ፣ አእምሮን የመቆጣጠሪያ ሥልቶችን አብዝቶና ጥበቡን አስፍቶ፤ ሃሌ-ሉያ.. እያለ ጉርሻ እየሰጠ መጣ። ተሳዳቢው መንፈስ፣ እልኸኛው መንፈስ፣ አጉረምራሚው መንፈስ፣ የቅዱሳንን መንፈስና ኃይል የሚያርቀው፣ የመልአክትን ጥበቃ የሚክደውና የሚያስወግደው መንፈስ፣ የድንግል ማርያምን አማላጅነት በምሥጢረ-ሥጋዌ የተባረክንባትን የቅድስናዋን መንፈስ ከሰው ልጅ የሚያርቀውና የሚያንኳስሰው የአውሬው መንፈስ፤ ከባሕር ውስጥ ወጣ።

**የሲኦሉ መንፈስ፤** ትምሕርትን፤ እውቀትን በአጠቃላይ ሳይንስን መሠረት አድርጎ፤ ምሁራንን የሚያሳድደው መንፈስ፣ በአእምሮ ውስጥ የጭንቀት፣ የብቸኝነትና፣ የጥርጣሬ ዘር እየዘራ፣ ትውልድን የሚያወድመው፣ ከሃይማኖት ጎዳና የሚያስወጣውና እምነትን የሚንደው የተጣለው መልአክ፤ የጨለማው ኮከብ ወይም የሉሲፈር መንፈስ፤ በሙያችን፣ በጥበባችንና በፍልስፍናችን ውስጥ ዘልቆ ገባ።

**በአጠቃላይ፤** የወንድሞቻችን ከሳሽ የተጣለው ዲያብሎስ፤ የጻድቃንን መንፈስ የሚቃወመው ኃይል፤ በውስጣችን ቦታና ሥፍራ ያዘ። የቤተክርስቲያንን ጉዞ የሚያቀጭጭ፣ ወደ ቤተክርስቲያን የሚገቡትን አቅጣጫቸውን የሚያስት፤ አገልጋዮችን መንፈሳቸውንና ሞገሳቸውን የሚያስጥል፤ የሰማያዊ ጸጋ በረከትን የመካፈል ጽድቃቸውን የሚያበላሽ፤ የወሬኝነት፣ የተቺነት፣ የተቃዋሚነት፣ የፌዘኝነት መንፈስ ዘልቆ ገባ። መናፍስት ከተጫኑውና ካጠቃው ዘር ተገኝተን፤ እንዴት የተቀደሰ ሃሳብ ለማመንጨትና የተባረከ ሥራ ለመሥራት አቅምና ጉልበት ይኑረን? እንዲህ ሆነን፤ ገና በለጋና በወጣትነት ዕድሜያችን፤ በክፉ መናፍስት እጅና እግራችን ተሳስሮና አካላችን ደቆ፤ ፈዘንና ደንግዘን **በማለዳ ተያዝን**።

**እንግዲህ እንዴት እናድርግ?** የሰዎች ልብ በጭካኔ ተመቷል። የምሁራኖች እምነት ከመንፈሳዊ አቅጣጫ ውጭ ወጥቶ የቀዘቀዘ ሆኗል። የሽማግሌዎች መንፈሳዊ በረከት-ተስፋ፤ ከቅድስና መለኮታዊ ምሪት ተቋርጧል። እግዚአብሔር አምላክ ቤት ውስጥ ስንኖር፤ ፈተናዎቻችን እጥፍ ድርብ በመሆን፤ መንፈሳዊውን ሕይወት የሚያጨናግፉ ችግሮች ሰፍተውብናል። መንገድ ላይ እየቀረን ነው። ዲያብሎስ በታላቅ ቁጣ ወደ ምድር ወድቆአል። እግዚአብሔር አምላክ ይማረን።

ISBN 978-99944-989-3-2
9 789994 498932 >

ዋጋው፤ አንድ መቶ ብር
USD 50.00

Graphic Printers